# የዱር እንስሳትና መኖሪያ አካባቢያቸው ጥናትና ምርምር ፈቃድ አሰጣጥ

# መመሪያ ቁጥር 851/2014

# የዱር እንስሳትና መኖሪያ አካባቢያቸው ጥናትና ምርምር ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 851/2014

ሀገሪቱ ያላትን ወደር የሌለው የዱር እንስሳት ሃብት በመጠበቅና በማልማት ዘለቄታዊ ጥቅም እንዲሰጥ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ዙሪያ እየተደረገ ያለውን ጥረት ውጤታማነት ለማሳደግ በጥናትና ምርምር መደገፍ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአገሪቱን የዱር እንስሳት ሀብትን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በመጠበቅ፣ በመንከባከብና በማልማት በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

የዱር እንስሳት ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀምን በሚመለከት ሀገሪቱ በአለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት የገባችውን ግዴታዎች በተቀናጀና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ለመፈጸም ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤

የዱር እንስሳት ጥናትና ምርምር በተጠና ስርዓትና ግልፅነት ባለው አሰራር በማከናወን የአገሪቷን መብትና ጥቅም በሚያስጠብቅ መልክ ማካሄድ ስለሚገባ፤

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 541/199 አንቀፅ 17/2 እና በደንብ ቁጥር 163/2001 አንቀጽ 8 በተደነገገው መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "የዱር እንስሳትና መኖሪያ አካባቢያቸው ጥናትና ምርምር ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 851/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1. **"አዋጅ"** ማለት የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 ነው፤
2. **"ደንብ"** ማለት የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2001 ነው፤
3. በአዋጅና ደንቡ አንቀጽ 2 ላይ የተገለፁ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም ተፈፃሚ ይሆናሉ
4. **"የዱር እንስሳት መኖሪያ አካባቢ"** ማለት  የየብስ፣ የውሃ አካል ወይም ሁለቱንም የሚያካትት ሆኖ የዱር ሕይወት የሚኖሩበት የዱር ሕይወት የጥበቃ ቦታ ወይም ከጥበቃ ቦታ ውጪ ያለ ሥፍራ ነው፤
5. **"ቡድን"** ማለት ሁለትና ከዛ በላይ አባላት ያሉት የጥናትና ምርምር የባለሙያዎች ስብስብ ወይም የጥናትና ምርምር ተቋም ነው፡፡
6. **"የቡድን መሪ"** ማለት በአንድ የተመራማሪዎች ቡድን የሚካሄድን የዱር እንስሳት እና መኖሪያ አካባቢያቸው ጥናትና ምርምር ተግባር በበላይነት የሚመራ ባለሞያ ነው፡፡
7. **"የፕሮጀክት ንድፍ"** ማለት ተመራማሪው ወይም ቡድኑ የጥናትና ምርምር ሥራ ለማከናወን የተቀረጸና ዝርዝር ተግባራትና የሥራውን መርሃ-ግብር ያካተተ ሰነድ ነው፡፡
8. **"ፈቃድ"** ማለት በዱር እንስሳቱና መኖሪያ አካባያቸው ላይ ጥናትና ምርምር ለማካሄድ ለተመራማሪ ወይም ቡድን  ከባለስልጣኑ በጽሑፍ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡
9. **"ድህረ ምረቃ ጥናት ፈቃድ"** ማለት ለኢትዮጵያዊያንና ለውጪ ተማሪዎች ለሁለተኛና ሦስተኛ ዲግሪ ማሟያ የሚሆን በኢትዮጵያ ዱር እንስሳትና መኖሪያ አካባያቸው ላይ ጥናት እንዲያደርጉ በባለሥልጣኑ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡
10. **"የጥናትና ምርምር ውጤት ሕትመት"** ማለት ለጥናት በመረጃ ምንጭነት ሊያገለግል የሚችል መረጃ የያዙ፣ ተገምግመው በሚታተሙ ሳይንሳዊ መጽሔቶች፣ በሞኖግራፍ፣ በመጻሕፍትና በተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ

ሚዲያዎች ላይ የሚወጣ ጥናታዊ ጽሑፍ ወይም አጠቃላይ የዱር እንስሳትና መኖሪያ አካባያቸውን የሚመለከቱ ግኝቶች ይዘትና ዝርዝር ጥናት የሚያካትት ህትመት ማለት ነው፡፡

11."**የፈቃድ ዓመት**" ማለት ለአንድ ተመራማሪ ወይም የምርምር ቡድን በፍቃድ ዘመን ውስጥ በየዓመቱ የሚታደስ ሆኖ ለአንድ ዓመት የሚሰጥ የፈቃድ ጊዜ ነው፡፡

12."**ማመልከቻ**" ማለት ጥናትና ምርምር የማድረግ ፈቃድ ለማግኘት ለባለሥልጣኑ የሚቀርብ ማመልከቻ ነው፡፡

13."**ክልል**" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬደዋ መስተዳድርን ይጨምራል፤

14.“**ሚኒስቴር**” ማለት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ነው::

15.“**ባለስልጣን**” ማለት የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ነው፡፡

16.ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀ አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

## 3. <u>የመመሪያው ዓላማ</u>

1. በዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ዙሪያ እየተደረገ ያለውን ጥረት በጥናትና ምርምር በመደገፍ የአገሪቱን የዱር እንስሳት ሀብት ሣይንሳዊ በሆነ መንገድ በመጠበቅ፣ በመንከባከብና በማልማት በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ፤
2. የዱር እንስሳት ጥበቃ፣ ልማትና አጠቃቀምን በሚመለከት ሀገሪቱ በአለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት የገባቸውን ግዴታዎች በተቀናጀ መልኩና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ለመፈጸም ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፤
3. የዱር እንስሳት ጥናትና ምርምር በተጠና ስርዓትና ግልፅነት ያለው አሰራር እንዲኖረውና የአገሪቷን መብትና ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ እንዲከናወን ማድረግ፤

## 4. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በውጭ ሀገር ዜጎችና በፌዴራል መንግስት በሚተዳደሩ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች በሚደረጉ ጥናትና ምርምር ስራዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የጥናትና ምርምር ዘርፎች፤ የፈቃድ ማመልከቻ ይዘትና መስፈርቶች

### 5. መሠረት

1. ማንኛውም የውጭ ዜጋ ተመራማሪ ወይም ቡድን በዱር እንስሳትና መኖሪያ አካባቢያቸው ጥናትና ምርምር ለማከናወን ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡
2. ማንኛውም በፌዴራል መንግስት በሚተዳደሩ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ጥናትና ምርምር የሚያከናውን ተመራማሪ ወይም ቡድን ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡
3. በክልሎች በሚተዳደሩ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ጥናትና ምርምር የሚያከናውን ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ተመራማሪ ወይም ቡድን ከክልሉ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ብርቅዬና ህልውናቸው ለአደጋ የተጋለጡት ዝርያዎች ላይ ጥናትና ምርምር የሚያከናውን ተመራማሪ ወይም ቡድን ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

### 6. ስለጥናትና ምርምር ማመልከቻ ይዘት

ማንኛውም የጥናትና ምርምር ፍቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡፡

1. የተመራማሪውን ወይም የቡድን መሪውን ሙሉ ስም፣ አድራሻ፣ ዜግነት፣የፓስፖርት ኮፒ፣
2. በጥናት ውስጥ የሚሳተፉ የቡድን አባላት ስም ዝርዝር፤
3. የሰለጠኑበት የሙያ ዘርፍና የትምህርት ደረጃቸውን የሚያመላክት ማስረጃ ኮፒ፣
4. የትምህርትና የሥራ ልምድ ማስረጃ (ሲቪ)፣
5. የሚሰሩበት ወይም የሚማሩበት ተቋም ስምና ሙሉ አድራሻ እንዲሁም የተቋሙ የድጋፍ ደብዳቤ፣

6. ስለ ቡድን መሪው ወይም ተመራማሪው ምሥክርነት ሊሰጡ የሚችሉ ጥናቱ በሚካሄድበት ዘርፍ በምርምር ሥራዎቻቸው የታወቁ ሦስት ባለሙያዎች ስምና ሙሉ አድራሻ፣
7. የጥናቱ ርዕስ፣ የጥናቱ መስክ ፣ ጥናቱ የሚፈጀው ጊዜ እና የጥናቱ አላማ ፣
8. የመስክ ጥናቱ የሚከናወንበት ጊዜ (ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት) ፣
9. ጥናቱ የሚካሄድበት ቦታ መጠሪያ፣
10. በጥናቱ ሂደት የሚመለሱ ዋና ዋና ጥያቄዎችና መላምቶች፣
11. የምርምር ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚጠቀምባቸው የጥናት ሥልቶች፣
12. ጥናቱን ለማካሄድ በመስክ የሚገለገልባቸውን ተሽከርካሪዎችና መሣሪያዎች፣
13. ጥናቱን ለማካሄድ የሚያስፈልገው የገንዘብ መጠንና ምንጭ፣
14. ጥናቱን ለማካሄድ የገንዘብ ድጋፍ የተጠየቀበት ኘሮፖዛል ኮፒ፣ እና
15. የገንዘብ ድጋፍ የሚሰጠው ድርጅት /ተቋም ገንዘቡን መስጠቱንና የተገኘውን ገንዘብ መጠን፡፡

## 7. <u>የጥናትና ምርምር ጥያቄ አቀራረብና ሂደት</u>

1. አንድ ተመራማሪ ወይም ቡድን ለመጀመሪያ ጊዜ የጥናትና የምርምር ጥያቄ ሲያቀርብ ስለሚያጠናው ጉዳይ ከአንድ ገጽ ያልበለጠ ፍሬ ጉዳዩን የሚያመለክት የጽሑፍ ጥያቄ ለባለስልጣኑ ማቅረብ ይጠበቅበታል፣
2. ባለሥልጣኑ የጥናቱን አስፈላጊነት በመገምገምና ለጥናት የተጠየቀው ቦታ ከዚህ ቀደም በሌሎች ተመራማሪዎች ያልተያዘ መሆኑን በማረጋገጥ ከሦስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ምላሽ ይሰጣል፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀስ 1 የቀረበው የጥናትና ምርምር ፈቃድ ጥያቄ ተቀባይነት ሲያገኝ የጥናትና ምርምር ፈቃድ የማመልከቻ፣ እና የጥናትና ምርምሩን ክፍያ በደንቡ መሰረት ፣ በብሔራዊ ባንክ በኩል ለባለስልጣኑ ክፍያ ይፈፀማል፤
4. አመልካቹ የጥናትና ምርምር ማመልከቻ ክፍያ መክፈሉ ሲረጋገጥ የጥናት መጠየቂያ ቅጹ እንዲሰጠው ይደረጋል፣
5. ማንኛውም ተመራማሪ ወይም ቡድን በፍቃድ ማመልከቻው ቅጽ ላይ የሚሞላቸው መረጃዎችና ከማመልከቻ ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ ማናቸውም ማስረጃዎች በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተጻፉና ጽሑፎቹም የተተየቡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

6. የጥናት ፈቃድ ጠያቂው በዚህ አንቀፅ የተጠቀሱትን ካሟላ፣ ቅጹንና ክፍያ የፈጸመበትን ደረሰኝ ወይም የሚመለከተውን የድጋፍ ደብዳቤ ከአስፈላጊው መረጃዎች ጋር በማያያዝ ለባለስልጣኑ ገቢ ያደርጋል፣
7. በቂና አሳማኝ ምክንያት ካልቀረበ በስተቀር ለአንድ የጥናት ዓመት የተከፈለ የማመልከቻም ሆነ የጥናትና ምርምር ክፍያ የሚያገለግለው ጥናቱ ይካሄዳል ተብሎ ለተጠየቀበት ዓመት ብቻ ነው፡፡

## 8. <u>የጥናትና ምርምር ፈቃድ መስፈርት</u>

ማንኛውም ተመራማሪ ወይም ቡድን የጥናትና ምርምር ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላትይኖርበታል፡፡

1. የጥናትና ምርምር ቡድኑ መሪና አባላት የትምህርት ዝግጅትና ብቃት እንዲሁም የምርምር ልምድ ሊካሄድ ከታቀደው ጥናትና ምርምር ዓይነት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው፤
2. ጥናትና ምርምሩን ለማካሄድ ያገኘውን የገንዘብ መጠን፣ የተሰጠበት የገንዘብ ዓይነት እንዲሁም ለምን ያህል ጊዜ እንደተሰጠው የሚያረጋግጥ ማስረጃ ገንዘቡን ካገኘበት ተቋም ማቅረብና ወደ ሀገር የሚያስገባቸውን ለጥናትና ምርምር የሚያገለግሉ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች ለባለሥልጣኑ ማስመዝገብ የሚችል፡፡
3. የጥናትና ምርምር ቡድን መሪው በመስኩ የሥራ ልምድ ያለው ለመሆኑ ምስክርነት ሊሰጡ የሚችሉ የመስኩ ባለሙያዎች ስምና አድራሻ ማቅረብ የሚችል፤
4. ከዚህ ቀደም በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር የሙያውን ሥነ-ምግባር የሚጻረር ሪኮርድ የሌለባቸው የቡድኑ አባላት መያዝ፤
5. ለመስክ ጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ ቁሶችና መሣሪያዎች ማሟላት፤
6. የሚቀርበው የጥናት ሥልት ቡድኑ ካለው የጥናት መሣሪያዎችና ከአባላቱ ሙያና እውቀት ጋር የሚጣጣም መሆን፤
7. ቡድኑ ጥናቱን ለማካሄድ ያገኘው የገንዘብ መጠን ከአባላቱ ብዛት፣ ከጥናቱ ዓይነት፣ በመስክ ከሚቆይበት ጊዜና ከተፈቀደለት የጥናት መስክ አንፃር በቂ መሆን፣›
8. የጥናትና ምርምር ቡድኑ ከመስክ ለሚያሰባስባቸው ናሙናዎች በቂ እና ደረጃውን የጠበቀ ማከማቻና ማቆያ ማሟላት፤

9. ቡድኑ ከባለስልጣኑ የሚመደቡለትን ኢትዮጵያውያን የጥናትና ምርምር ባለሙያዎች በምርምር ሥራ ውስጥ የሚያሳትፍና አቅም መገንባት የሚችል፤
10. ጥናቱን በሚያካሂድበት ቦታ ለአደጋ የተጋለጡ የዱር እንስሳትና መኖሪያ አካባቢዎች ላይ ጥንቃቄ የሚያደረግና ኃላፊነት የሚወስድ፤
11. ተመራማሪው ወይም ቡድኑ አዲስ የጥናት ፈቃድ ለማግኘት ጥያቄ ቢያቀርብ ቀደም ሲል በተፈቀደለት ቦታ ላይ የጀመረውን ጥናትና ምርምርን በሚመለከት በተሰጠው ፈቃድ መሠረት በቂ መረጃ የሚሰጡ ሳይንሳዊ ጽሑፎችን የሚያሳትም፣
12. የጥናትና ምርምር ሥራውን በሀገሪቱ ሕግ መሠረት የሚያከናውንና እና ለባለሥልጣኑ የአቅም ግንባታ አስተዋጽኦ የሚያደርግ፤

## 9. <u>ስለድህረ ምረቃ ጥናት ፈቃድ</u>

1. የድህረ ምረቃ ጥናት ፈቃድ ማመልከቻ የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርበታል፡-
   - ሀ. የአማካሪ መምህር ስም፣ የትምህርት ተቋም ስም፣ የሚከታተሉትን የትምህርት ዓይነት፣ የመመረቂያ ጽሑፋቸውን ርዕስ፣ የጥናቱ ስልት፣የጥናቱ አላማ ፣ ጥናቱ የሚፈጀው ጊዜ፣ ለጥናቱና ምርምሩ ማስኬጃ የተገኘ የገንዘብ መጠን፤
   - ለ. የቀረበው የጥናት ጥያቄ ማመልከቻ አመልካቹ ከሚከታተለው የትምህርት ዘርፍ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው መሆኑን፤
   - ሐ. የተማሪው አማካሪ በመስኩ የሠለጠነና በቂ ልምድ ያካበተ መሆኑን፤፡
2. የድህረ ምረቃ ጥናት ጥያቄ አቀራረብ የሚፈፀመው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1-6 በተጠቀሰው መሠረት ይሆናል፡፡
3. የድህረ ምረቃ ጥናት የሚሰጠው የፈቃድ ጊዜ ከአራት ዓመት ያልበለጠ ይሆናል፡፡ ሆኖም ተማሪው ከአቅሙ በላይ በሆነ ችግር ምክንያት ጥናቱን ማቋረጡን የሚያስረዳ በቂ ማስረጃ ከሚማርበት ተቋም ካቀረበ የጥናት ጊዜው ለአንድ ዓመት ሊራዘምለት ይችላል፡፡
4. ተማሪው ለጥናቱ የተፈቀደለት ጊዜ ካበቃበት ቀን ጀምሮ ቦታው ለአንድ ዓመት ለሌላ አጥኚ አይሰጥም፡፡ ነገር ግን የአንድ ዓመት የጊዜ ገደቡ ካበቃ በኋላ ቀጣይ ጥናት ማድረግ ቢፈልግ ተማሪው ከሌሎች አጥኚዎች ቅድሚያ ለማግኘት በቅድሚያ ማመልከት ይኖርበታል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ግምገማና ፈቃድ አሰጣጥ

### 10. የጥናትና ምርምር ግምገማና ፈቃድ አሰጣጥ

1. ባለስልጣኑ በዚህ መመሪያ የተጠቀሱት የጥናትና ምርምር ማመልከቻውን ይዘትና መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ ገምግሞ ውጤቱን ያሳውቃል፡፡
2. ለግምገማ የቀረበ ማመልከቻ ያልተሟላ ሆኖ ከተገኘ ጥያቄውን ላቀረበው ተመራማሪ ወይም ቡድን መሪ መጠይቁን አሟልቶ ወይም አስተካክሎ እንዲያቀርብ በባለስልጣኑ በኩል ይገለጽለታል፡፡ ምላሽ በተሰጠው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መጠይቁን አሟልቶ ካላቀረበ ጥያቄው ይሰረዛል፡፡
3. የጥናትና ምርምር ፈቃድ፤ የአመልካቹን ስም፣ የጥናትና ምርምር ቡድኑ ስም፣ የጥናቱ ርዕስ፣ ፈቃድ የተጠየቀበትና የተሰጠበትን ቀን፣ ፈቃዱ የተሰጠበትን የጥናት መስክ፣ ጥናቱ የሚካሄድበትን ቦታ፣ ፈቃዱ ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ፣ ፈቃዱን የሰጠው አካል ስም ፊርማና ማህተም ይኖረዋል፡፡

### 11. ስለፈቃድ እድሳት

1. የዱር እንስሳት እና መኖሪያ አካባቢያቸው ጥናትና ምርምር የፈቃድ እድሳት ጥያቄ ቀደም ሲል የተሰጠው ፈቃድ ከመጠናቀቁ ከ2 ወር በፊት በግንባር በመቅረብ፣ በፖስታ፣ በኢ-ሜይል ወይም በድህረ ገጽ በመላክ ለባለስልጣኑ መቅረብ አለበት፡፡
2. ከአንድ ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ ፈቃድ የተሰጠው ተመራማሪ ወይም ቡድን ፈቃድ ካገኘ በኋላ አቅርቦት በነበረው የጥናት ማመልከቻ መሠረት ጥናቱን በትክክል ስለማከናወኑ በሚቀርቡ የመስክ ሪፖርቶች ተገምግሞ ሲረጋገጥ በየዓመቱ አስፈላጊውን ክፍያ በመፈፀም የማመልከቻ ቅጹን ሞልቶ ፈቃዱ ይታደሳል፡፡
3. ከአንድ ዓመት በላይ በመስክ የሚካሄድ የዱር እንስሳት እና መኖሪያ አካባቢያቸው ጥናትና ምርምር ፈቃድ በየዓመቱ መታደስ አለበት፡፡

12. <u>ፈቃድ ስለመሰረዝ</u>

ፈቃድ ሊያሰረዙ የሚችሉ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ፈቃድ በተሰጠ በስድስት ወር ውስጥ ጥናቱን ካልጀመረ ፣
2. ፈቃድ የተሰጠው አካል በፈቃዱ መሠረት በአግባቡ እየሰራ አለመሆኑ ሲረጋገጥ፣
3. የተሰጠው ፈቃድ ከአላማው ውጭ እየተሰራበተ መሆኑ ሲረጋገጥ፣
4. በዱር እንስሳቱና መኖሪያ አካባቢያቸው ላይ አደጋ ሊያመጣ የሚችል አሠራር መኖሩ ሲረጋገጥ፡፡
5. በዚህ መመሪያም ሆነ በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች የተጣለበትን ግዴታ በአግባቡ አለመወጣቱ ሲረጋገጥ፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የተመራማሪዎችና የቡድን መብትና</u>

## <u>ግዴታዎች</u>

13. <u>ተመራማሪ ወይም የቡድን መብቶች</u>

ማንኛውም ቡድን ወይም ተመራማሪ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡፡

1. አንድ ተመራማሪ ወይም ቡድን በተሰጠው የጥናት ፈቃድ ዘመን ውስጥ ከመስክ ባሰባሰባቸው መረጃዎች ላይ ያደረገውን የጥናት ውጤት የማሳተም ብቸኛ ባለመብት ይሆናል፡፡
2. በባለሥልጣኑ የጥናት ፈቃድ ተሰጥቶት የፈቃድ ዘመኑን ያላጠናቀቀ ተመራማሪ ወይም ቡድን ለጥናት ከመስክ ባሰባሰባቸው መረጃዎች ላይ ካለ ተመራማሪው ወይም ቡድኑ ዕውቅናና ፈቃድ በሦስተኛ ወገን ተመሳሳይ ጥናትና ምርምር እንዳይካሄድበት ወይም በቅጅ መልክ እንዳተላለፍ ይደረጋል፡፡

14. <u>የተመራማሪው  ወይም የቡድኑ ግዴታዎች</u>

ማንኛውም ተመራማሪ ወይም ቡድን የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፤

1. የጥናት ፈቃድ ተሰጥቶት የመስክ ሥራውን ፍቃዱ ከተሰጠው ቀን ጀምሮ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ጥናቱን የመጀመር፤

2. የውጭ ዜጋ ተመራማሪ ወይም ቡድን በመስክ ላይ የጥናትና ምርምር በሚያከናውንበት ወቅት ባለሥልጣኑ ለክትትልና ግምገማ ለሚያሰማራቸው ባለሙያዎች አስፈላጊውን ትብብር የማድረግ፣
3. ከአንድ እስከ ሶስት ዓመት ለሆነ የፈቃድ ዘመን በሚከናወን ጥናትና ምርምር ውስጥ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው የሥልጠና መመሪያ መሠረት የሚመደብለትን አንድ የዱር እንስሳ ባለሙያ በረዥም ጊዜ ትምህርት የማሰልጠን፣
4. ለጥናቱ በጊዜያዊነት የሚከራያቸው ንብረቶችን ፈቃድ ካላቸው ድርጅቶች የመከራየት
5. ጥናቱ በሚካሄድበት አካባቢ የሚኖረውን ህብረተሰብ ወግ፣ ባህልና እምነት የማክበር፣
6. ከባለስልጣኑ ተወካይና ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር ያለው የዕለት ተዕለት የሥራ ግንኙነት ሙያዊ ሥነ ምግባርን የተላበሰ እንዲሆን የማድረግ፣
7. በጥናትና ምርምር ማመልከቻ ስማቸው ያልተጠቀሱ አባላትን ባለሥልጣኑ ሳያውቀውና በጽሑፍ ሳይፈቀድ በጥናቱ ውስጥ ያለማሳተፍ፣
8. በዱር እንስሳትና መኖሪያ አካባቢያቸው አደጋ ሊያመጣ ከሚችል አሠራር የመታቀብ፣
9. የግማሽ ዓመቱን የመስክ ጥናት ካጠናቀቀ በኋላ የመስክ ሥራ ሪፖርት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የማቅረብ፣
10. ለጥናቱ የሚያስፈልጉ ናሙናዎችን ከሀገር ከማስወጣቱ በፊት የባለሥልጣኑን ልዩ ፈቃድ የማግኘት፣
11. በመስክ ጥናትና ምርምር ወቅት በተገኙ ውጤቶች ላይ በሌላ አካል ጋዜጣዊ መግለጫ /ፕሬስ ሪሊዝ/ ከመስጠቱ በፊት በቅድሚያ በባለሥልጣኑ በኩል በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሰጥ የማድረግ፣
12. ካሳተማቸው የጥናት ውጤቶች ሦስት ኦሪጅናል ቅጂዎችን ለባለሥልጣኑ የመስጠት፣
13. ለባለሥልጣኑ የሚቀርቡ ሪፖርቶች፣ የጥናት ዶክመንቶችና የህትመት ውጤቶች በእንግሊዝኛ ያልተዘጋጁ ከሆነ ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ አስተርጉሞ የማቅረብ፣
14. ስለዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የወጡትን ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች የማክበር፡፡

## ክፍል አምስት

## ተግባርና ኃላፊነት

### 15. የባለስልጣኑ ተግባርና ኃላፊነት

1. ለጥናትና ምርምር የሚቀርቡ ማመልከቻዎች በተሟላ ሁኔታ ሲቀርቡ ፈቃድ ይሰጣል፡፡
2. የጥናትና ምርምር ሥራዎች በሀገሪቱ ሕግ መሠረት መካሄዳቸውን ያረጋግጣል፡፡
3. ከተመራማሪው ወይም ከቡድኑ ጋር በተገባው ውል መሠረት የመጀመሪያው የጥናትና ምርምር ምዕራፍ ከተጠናቀቀ በኋላ የፈቃድ ዕድሳት ሲጠየቅ በተመራማሪው ወይም ቡዱኑ የሚቀርቡ የመሥክ ሥራ ሪፖርቶችና የጥናት ውጤቶች እንዲሁም የባለስልጣኑ ተወካይ የሚያቀርበውን ሪፖርት መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
4. በመስክ ሥራ ወቅት በክልል ቢሮዎች፣ በባለስልጣኑ ተወካይ ወይም በተመራማሪዎች በሚቀርቡ ሪፖርቶች ውስጥ የተመለከቱ ቅሬታዎችንና አቤቱታዎችን፣ አለመግባባቶችንና ግጭቶችን እንዲሁም የመመሪያ ጥሰቶችን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
5. በመስክ ሥልጠና የሚወስዱ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎችን ከባለስልጣኑ ባለሙያዎች፣ ከሀገር ውስጥ የትምህርት ተቋማትና ከክልል ቢሮዎች ይመርጣል፡፡
6. ከተመራማሪዎች ጋር በመስክ የክትትልና ቁጥጥር ሥራ የሚያከናውን ባለሙያ የሠለጠነበት የትምህርት ዓይነት ከሚካሄደው የመስክ ጥናት ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያለው መሆኑንና ከዚህ በፊት በመስክ ተመድቦ ሲሰራ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ የተወጣና የሥነ ምግባር ጉድለት የሌለበት መሆኑን አረጋግጦ ይመድባል፡፡
7. የተመራማሪዎችን ዝርዝር የያዘ የትብብር ደብዳቤ አዘጋጅቶ ጥናቱን ለሚያካሂድበት ክልል ይልካል፤ የውጭ ዜጋ ለሆኑ ተመራማሪዎች የፓስፖርት ቁጥራቸውንና ዜግነታቸውን በመጥቀስ የይለፍና የመኖሪያ ፈቃድ እንዲያገኙ ለሚመለከተው አካል ይጽፋል፡፡
8. ጥናትና ምርምሩ የሚደረግበት ክልልና የአካባቢው ማህበረሰብ በጥናትና ምርምር ተጠቃሚ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

9. የባለስልጣኑን የመስክ ተወካይ ተግባርና ኃላፊነት ይቆጣጠራል፡፡

## ክፍል ስድስት
## ስለ ንብረቶች አገባብ፣ አያያዝና አጠቃቀም

16. **የጥናትና ምርምር ንብረቶች ስለሚገቡበት ሁኔታ**

የጥናትና ምርምር መገልገያ መሣሪያዎችና ንብረቶች ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡት በሀገሪቱ ሕግ መሠረት ይሆናል፡፡

17. **ስለጥናትና ምርምር ንብረቶች አያያዝ**

1. በጥናትና ምርምር ስም በባለሥልጣኑ አማካኝነት ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡት ንብረቶች አያያዝ የመንግሥትን ህግና ደንብ ተከትሎ ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀስ 1 መሠረት አጥኚውና ባለሥልጣኑ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ የጥናትና ምርምር መሣሪያዎች እንዳይበላሹና ጉዳት እንዳይደርስባቸው ተገቢውን እንክብካቤ ያደርጋሉ፤ ከተበላሹም ያሰራሉ፡፡
3. በጥናትና ምርምር ስም የሚገቡ መሣሪያዎችና ተሽከርካሪዎች ዓመቱን ሙሉ የሚሸፍን የመድን ዋስትና በአጥኚው ወይም በቡድኑ የተገባላቸውና በህጋዊ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ መሆን አለባቸው፡፡

## ክፍል ሰባት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

18. **የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ይህንን መመሪያ በማስፈጸም ረገድ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

19. **ቅሬታ ስለማስተናገድ**

1. በፈቃድ አሠጣጥም ሆነ መሠረዝ ምክንያት ቅር የተሰኘ ማንኛውም ተመራማሪ ወይም ቡድን ቅሬታውን በ30 ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. በባለሥልጣኑ መልስ ያልተስማማ ቅሬታ አቅራቢ አቤቱታውን ለሚኒስቴሩ ማቅረብ ይችላል፡፡

20. **ቅጣት**

ይህንን መመሪያ የሚተላለፍ ማንኛውም ሰው አግባብነት ባለው ሕግ ይቀጣል፡፡

21. **የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት የጥናትና ምርምር ፈቃድ ተሰጥቷቸው ጥናታቸውን የጀመሩ ተመራማሪዎች ወይም ቡድኖች መመሪያው ተግባራዊ ከሆነበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ጥናታቸውን መቀጠል ይችላሉ፡፡

22. **ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች**

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በመመሪው በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

23. **መመሪያውን ስለማሻሻል**

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

24. **መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከሰኔ 1 ቀን 2007 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡